ጋዜጣዊ መግለጫ

ሰኔ 25, 2015 ዓ.ም

ፕረስ ሪሊዝ

አሁኑኑ የሚለቀቅ

**የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ለማሻሻል የትምህርት ባለድርሻዎችንና ህብረተሰቡን ያሳተፈ አገር አቀፍ ህዝባዊ ንቅናቄ በይፋ ተጀመረ**

ሰኔ 25/2015 ዓ.ም  አዲስ አበባ

ትምህርት ሚኒስቴር የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት ለማሻሻል "ትምህርት ለትውልድ" በሚል መሪ ቃል ሀገር አቀፍ ህዝባዊ ንቅናቄ ማስጀመሪያ መርሃ-ግብር ከፍተኛ የመንግስት የስራ ሃላፊዎች፣ ባለሀብቶች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ አርቲስቶች፣ የትምህርት ማህበረሰቡ አባላት፣ የልማት ድርጅቶች እና ሌሎች ባለድርሻ አካላት በተገኙበት ሰኔ 25/2015 ዓ.ም በአዲሱ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ ዋና መስሪያ ቤት ይፋ ተደረገ።

የሀገራዊ ንቅናቄው ዓላማ በየደረጃው ባለው ማህበረሰብና ልዩ ልዩ አካላት ተሳትፎ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት ለማሻሻል የአሠራር ሥርአት ተዘርግቶ ሥራው በዘላቂነት እንዲቀጥልና ማህበረሰቡ የመማር ማስተማሩን ሂደት በባለቤትነት እንዲደግፍ ለማስቻል ነው፡፡

በዚህ ሀገር አቀፍ ንቅናቄ በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ በውጭ ሀገራት የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ ወዘተ. በትውልድ ቦታቸው፣ በተማሩበት ቦታ፣ ማህበራት፣ የግልና የመንግሥት ተቋማት፣ የልማት አጋሮች በሚሰሩባቸውና በሚኖሩባቸው አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች መሰረተ -ልማቶችን ለማሟላት በሚችሉት መንገድና መጠን አስተዋጽኦ በማድረግ አሻራቸውን የሚያሳርፉበት ሁኔታ ተመቻችቷል።

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

CamScanner

የትምህርት ሚኒስትሩ ፕሮፌሰር ብርሀኑ ነጋ የትምህርት ቤቶችን መሰረተ ልማት የማሻሻል ስራ ለመንግስት ብቻ የተተወ ኃላፊነት አለመሆኑንና በየደረጃው ያለው ማህበረሰብና ልዩ ልዩ አካላት ተሳትፏቸውን ሊያሳድጉ እንደሚገባ ገልፀው "ገንዘብ ያለው በገንዘቡ፣ ሀሳብ ያለው በሀሳቡ፣ ጉልበት ያለው በጉልበቱ" የሚችለውን ሁሉ አስተዋጽኦ እንዲያደርግ ጥሪ አስተላልፈዋል፡፡ አገር አቀፍ ንቅናቄውም ህብረተሰቡ የትምህርት መሠረተ–ልማትን በማሻሻል የመማር ማስተማሩን ሂደት በባለቤትነት እንዲደግፍ ለማድረግ መሆኑን ተናግረዋል።

የትምህርት ጥራት ችግሮች መንስኤዎች ዘርፈ ብዙ ቢሆኑም፤ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ምቹ አለመሆናቸው ከመሰረታዊ ችግሮች አንዱና ዋነኛው ነው። በዚህም በሀገራችን ከ50ሺ በላይ ከሚሆኑ ትምህርት ቤቶች ውስጥ ከ86% በላይ የአንደኛና የመካከለኛ ደረጃ ት/ቤቶች እንዲሁም ከ71% በላይ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች ለመማር ማስተማር አስፈላጊ የሆኑ መሠረተ–ልማቶች በተሟላ ደረጃ ስለሌላቸው ተማሪዎች በተጓደለ የትምህርት ከባቢ ውስጥ እንዲማሩ ተገደዋል።

በሃገሪቱ ካሉት ትምህርት ቤቶች 33.2% አንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶችና 55.67% ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው የንጹህ መጠጥ ውሃ አገልግሎት ያላቸው። ከዚህ ውስጥም 21.3% በአንደኛና መካከለኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች እንዲሁም 49.1% የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በቀጥታ የቧንቧ ውሃ ተጠቃሚ መሆናቸውን እና የተቀሩት ትምህርት ቤቶች ምንም አይነት የውሃ አቅርቦት እንደሌላቸው መረጃዎች ያመላክታሉ።

በትምህርት ቤቶች የመፀዳጃ ቤት አገልግሎትን በተመለከተም 37% አንደኛና መካከለኛ ደረጃ እንዲሁም 43% ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ የመፀዳጃ አገልግሎት የሚሰጡ ሲሆን ከ ኤሌክትሪክ አቅርቦት አንፃርም 29.4% አንደኛ እና መካከለኛና 74.5% ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ብቻ ናቸው ተጠቃሚ የሆኑት።

የትምህርት ፋሲሊቲና ግብዓቶችን በማሟላት ትምህርት ቤቶች ስታንዳርዱን ጠብቀው እንዲመሰረቱ ከማድረግ አንፃር ሰፊ ክፍተት ያለ በመሆኑ ከግብዓት አንፃር መሰረታዊ የሚባል ክፍተት አለባቸው።

በፕሮግራሙም ትምህርት ቤቶቹን የማሻሻል ስራ የተሳለጠ ለማድረግ በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ለአጠቃቀም ምቹና ቀላል ዌብ–ፖርታል (sip.moe.gov.et) ተዘጋጅቶ ከዛሬ ጀምሮ አገልግሎት እንዲሰጥ ተደርጓል።

**የሕዝብ ንቅናቄው ዋና ዓላማ**




CamScanner

የትምህርት ጥራት ችግሮች መንስኤዎች ዘርፈ ብዙ ቢሆኑም፣ ትምህርት ቤቶች ለመማር ማስተማር ምቹ አለመሆናቸው ከመሰረታዊ ችግሮች አንዱና ዋነኛው ነው። ከደረጃ በታች በሆኑ ት/ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች የሚጠበቅባቸውን እውቀት፣ ክህሎትና የባህሪ ለውጥ ማምጣት አለማስቻላቸው በግልጽ ታይቷል፡፡

ይህን ችግር በመንግሥት አቅም ብቻ ለመፍታት ቢታሰብ ከሶስት አስርት አመታት ያላነሰ ጊዜ ሊወስድ ይችላል። ስለዚህ ይህን ሰፊ ችግር መፍታት የሚቻለው ሥርዓት አበጅቶ በዘላቂነት የማህበረሰብና የልዩ ልዩ የትምህርት ባለድርሻ አካላት ማለትም በየደረጃው ያሉ አመራሮች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ፣ የቀድሞ ተማሪዎች፣ ታዋቂ ግለሰቦች፣ በውጭ አገር የሚኖሩ ኢትዮጵያውያንና ትውልደ ኢትዮጵያውያን፣ ባለሀብቶች፣ ወዘተ. በትውልድ ቦታቸው፣ በተማሩበት ቦታ፣ በሚሰሩባቸውና በሚኖሩባቸው አካባቢ የሚገኙ ትምህርት ቤቶች መሰረተ-ልማቶችን ማሻሻል ሲቻል ነው፡፡ በመሆኑም እነዚህን ትምህርት ቤቶች በሕዝብ ንቅናቄ አግባብ ለማሻሻል እቅድ ተዘጋጅቷል፡፡ የዚህ የሕዝብ ንቅናቄው ዋና ዓላማ በየደረጃው ያሉ ማህበረሰብና ልዩ ልዩ አካላትን በማሳተፍ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት ለማሻሻል እንዲሁም በዘላቂነት የመማር ማስተማርን ሂደቱን በቀጣይነት በባለቤትነት እንዲደግፍ ለማስቻል ነው፡፡

## በሀገራዊ ንቅናቄው የሚጠበቁ ውጤቶች

- የሕዝብ ንቅናቄ አደረጃጀት በመፍጠር ወደ ተጨባጭ ሥራ መግባት፣ ትምህርት ቤቶችን ማሻሻል፡፡
- የትምህርት ቤቶችን ነባራዊ ሁኔታ መለየት፣ እንዲሻሻሉ ማድረግ፡፡
- በየደረጃው ባለው ማህበረሰብና ልዩ ልዩ አካላት ተሳትፎ የትምህርት ቤቶችን መሠረተ-ልማት ለማሻሻል የየራሳቸውን ድርሻ በሃላፊነት መወጣት፡፡
- የትምህርት ቤት መሠረተ-ልማት ለማሻሻል የአሠራር ሥርአት በመዘርጋት በዘላቂነት እንዲቀጥል ማደረግ፡፡
- ማህበረሰቡና ልዩ ልዩ አካላት በሙያቸው፣ በእውቀታቸውና በጉልበታቸው አስተዋጽኦ ማድረግ፡፡
- በማህበረሰቡና በልዩ ልዩ አካላት ተሣትፎ የትምህርት ቤቶች መሠረተ-ልማቶች ማሻሻል፡፡

## ስለ ትምህርት ሚኒስቴር

የትምህርት ሚኒስቴር በአስፈጻሚ አካላት ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1263/2014 መሠረት በአጠቃላይና ከፍተኛ ትምህርት ዘርፎች የተዋቀረ መሥሪያ ቤት ሲሆን በአጠቃላይ ትምህርት ዘርፍ ከ49ሺ በላይ የሚሆኑ የቅድመ

አንደኛ፣ የአንደኛ ደረጃ፣ የመካከለኛና የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶችን እንዲሁም በከፍተኛ ትምህርት ዘርፍ 47 ከፍተኛ የትምህርት ተቋማትን፣ የትምህርትና ሥልጠና ባለስልጣን እና የትምህርት ምዘናና ፈተናዎች አገልግሎትን የያዘ ነው::

ተግባርና ኃላፊነቶቹም የአጠቃላይና የከፍተኛ ትምህርት፣ ፖሊሲዎችን፣ ስትራቴጂዎች፣ ህጎች እና ፕሮግራሞች መቅረጽ፤ የሥርዓተ–ትምህርት ማዕቀፍ ማዘጋጀት፤ የትምህርት እና የትምህርት ተቋማትን ስታንዳርድ ማውጣት፤ ሀገራዊ የብቃት ማዕቀፍ ማዘጋጀትና በሥራ ላይ መዋሉን ማረጋገጥ፤ የትምህርትና ሥልጠና ፖሊሲውን መሠረት መተግበር፤ ሀገር አቀፍ ፈተናዎች ማዘጋጀትና ጥራትን ማረጋገጥ፣ የፈፃሚን አቅም መገንባትና ክትትልና ድጋፍ ማድረግ፣ ወዘተ. ያካትታል፡፡

## ስለፖርታሉ

በትምህርት ሚኒስቴር የተዘጋጀው ዌብ–ፖርታል ለአጠቃቀም ቀላልና  ምቹ እንዲሁም በሀገሪቱ ውስጥ የሚገኙ 49 ሺህ የሚጠጉ ት/ቤቶችን መረጃዎች በአግባቡ ሰንዶ የያዘ ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ሲሆን ለጋሾች፣የቀድሞ ተማሪዎች፣ ባለሀብቶች፣ የአካባቢው ማህበረሰብ አካላት ወ.ዘ.ተ. ለማገዝ የሚፈልጉት አካባቢና ት/ቤት ምን ይጎድለዋል የሚለውን ጥያቄ በቀላሉ የሚመልስ ነው፡፡

ይህ ፖርታል በሀገራችን ያሉ ትምህርት ቤቶችን አጠቃላይ መረጃ የያዘ ከመሆኑም በተጨማሪ በየጊዜው የሚደረጉ የት/ቤቶች መሻሻሎችን የሚያሳይም ነው ፡፡

ጥራት ያለው ትምህርት ለሁሉም!

ትምህርት ሚኒስቴር

ዌብሰይት : Ministry of Education Ethiopia (moe.gov.et)

ዌብ–ፖርታል : SIP Campaign (moe.gov.et)

ፌስቡክ: https://www.facebook.com/fdremoe

ለተጨማሪ መረጃ


ስም – 1. እሴተ የሺጥላ

ለሚኒስትሩ ከፍተኛ የኮሙኒኬሽን አማካሪ


በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ትምህርት ሚኒስቴር Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

CamScanner

ስልክ–0911235322

ኢ–ሜል– esete.yeshitla@ethernet.edu.et

2. ስም– አመለወርቅ ህዝቅኤል

የህዝብ ግንኙነትና ኮሙኒኬሽን ስራ አስፈጻሚ

ስልክ– 0911976196

ኢሜል– amelehizkeal@gmail.com

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የትምህርት ሚኒስቴር
Federal Democratic Republic Ethiopia Ministry of Education

CamScanner